# ዶር ነጋሲና አቶ ስዬ አንድነትን ተቀላቀሉ - ኢትዮጵያዊነት እያሸነፈ ነዉ !

ግርማ ካሳ (ቺካጎ)
muziky68@yahoo.com

*«ኢትዮጵያዉያንን እስከሆንን ድረስ ትግራይ መሬታችን ነዉ። ኦሮሚያ መሬታችን ነዉ። ደቡብ ና ሶማሊያ መሬታችን ነዉ። አፋርም መሬታችን ነዉ። ለነርሱም ትግራይ መሬታቸዉ ነዉ። አማራም ትግራይ መሬቱ ነዉ። ሊኖርበት ይችላል። በዚህ ማመን አለብን። ከዚህ ዉጭ የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶችን እንደጠላት ለማስፈራሪት መጠቀም የሥልጣን እድሜን ማራዘሚያ እንደሆነ መታወቅ አለበት። አሁንም በሰላምዊ ትግል ካመኑትና ሕጋዊ ፈቃድ ካገኙት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር አብረን መሥራት እንቀጥላለን።"*
አቶ ገብሩ አሥራት

**«ኢትዮጵያ እኮ የኢሕአዴግ ብቻ አይደለችም። ኢትዮጵያ የእኛም ናት»**
አቶ ቡልቻ ደመቅሳ

**«ኢትዮጵያችን»**
ዶር መራራ ጉዲና

ኅዳር 19 ቀን 2002 ዓ.ም

አቶ ስዬ አብርሃና ዶር ነጋሶ ጊዳዳ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የሚመራዉን የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ መቀላቀላቸዉን በተመለከተ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተለያዩ አስተያየቶች እየተሰጡ ነዉ።

አስተያየቶቹ በጥቅሉ ብንመለከታቸዉ በሶስት ምድብ የሚከፈሉ ናቸዉ። የመጀመሪያዉ ምድብ የአብዛኛዉን ኢትዮጵያዊ ስሜት ያንጸባርቃል ብዬ የማስብሰዉ፣ በአቶ ስዬ አብርሃና በዶር ነጋሶ ጊዳዳ ዉሳኔ የተደሰቱ ኢትዮጵያዉያን አስተያየቶችን የያዘ ምድብ ነዉ።

ሁለተኛዉ ምድብ አቶ ስዬና ዶር ነጋሶ የቀድሞ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ከመሆናቸዉ የተነሳ የአንድነት ፓርቲን መቀላቀላቸዉ ያላስደሰታቸዉ ወገኖች አስተያየቶችን የያዘ ምድብ ነዉ። በዚህ ምድብ ያሉ የተቃዉሞ አስተያየቶች በብዛት በኢትዮጵያ ያለዉን የፖለቲካ ሁኔታ ከግምት ዉስጥ ያስገቡ፣ በጠራ አይምሮ ታስበዉና ተወጥነዉ የወጡ ተቃዉሞዎች ሳይሆኑ ከግለሰባዊ ስሜትና ከቂም በቀል መንፈስ የመነጩ ተቃዉሞዎች ናቸዉ። «እነ አቶ ስዬ ከዚህ በፊት የገዢዉ ፓርቲ ባለሥልጣናት የነበሩ ጊዜ ላጠፉት ጥፋቶች ተጠያቂ መሆን ይገባቸዋል። ወንጀለኞች ናቸዉና እንዴት የአንድነት ፓርቲ እነርሱን ይቀበላላል» ይላሉ።

እርግጥ ነዉ አቶ ስዬም ሆነ ዶር ነጋሶ የኢሕአደግ ባለሥልጣናት እንደመሆናቸዉ ኢሕአዴግ ላጠፋዉ ጥፋቶች እነርሱም ተጠያቂዎች ናቸዉ። ነገር ግን ከኢሕአዴግ አመራሮች ጋር ባሏቸዉ ልዩነቶች ምክንያት ኢሕአዴግን ጥለዉ ወጥተዋል። ባለሥልጣናት ሆኖ በመቀጠል፣ ሕሊናቸዉን ሸጠዉ መኖር ሲችሉም ኢሕአዴግ የሚያራምዳቸዉን አንዳንድ ፖሊሲዎች በመቃወማቸዉ እነርሱም የኢሕአዴግ በተር ደርሶባቸዉ እንደነበረ የሚታወስ ነዉ።

በኢሕአደግነታቸዉ ሳይሆን በግለሰብ ደረጃ ወንጀል ሰሩ ከተባለ ደግሞ እንደማንም ዜጋ ለፍርድ መቅረባቸዉ አይቀርም።

የአንድነት ፓርቲ በመጀመሪያ ደረጃ በኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት እንዲኖር የሚታገል ድርጅት ነዉ። የሕግ የበላይነት ስንል አንድ ሰዉ ነጻ በሆነ ፍርድ ቤት ተከሶ፣ እራሱን በነጻነት የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት **ፍርድ ቤት ወንጀለኛ እስኪለዉ ድረስ ወንጀለኛ አይደለም።** (innocent until proven guilty) ስለዚህ አቶ ስዬንም ሆነ ዶር ነጋሶን በግላቸዉ ወንጀለኛ ናቸዉ ብሎ አሁን መፍረድ ትልቅ

ስህተት ነዉ።

ከላይ እንዳልነዉ ወንጀል ሰሩ ከተባለ ለፍርድ መቅረብ ይኖርባቸዋል። እነርሱም በማናቸዉም ጊዜ ፍርድ ቤት ለመቅረብ ዝግጁ እንደሆኑ በይፋ ገልጸዋል። አድራሻቸዉን እናውቀዋለን። ሸሽተዉ አገር ጥለዉ አልሄዱም። ስለሆነም መካሰሱንና መወነጃጀሉን ለባለሞያዎችና ለዳኞች ትተን በእርቅ በይቅርታ በመቀባበልና በአንድነትን አገራችንን የምናድንበት ጊዜ ነዉ ባይ ነን።

አንድ ጊዜ አንዲት ሴት አመነዘረች ብለዉ በድንጋይ ሊወግሯት ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አመጧት። «ስለዚች ሴት ምን ትላለህ ? » ብለዉ ጠየቁት። እርሱም ሴትየዋ አላጠፋችም ብሎ አልመለሰላቸዉ። ነገ ግን »ከናንተ ሐጢያት የሌለበት የመጀመሪያዉን ድንጋይ ይወርዉር » አላቸዉ። ሕሊናቸዉ እየወቀሳቸዉ አንድ በአንድ የሴትየዋ ከሳሾች ስፍራዉን ጥለዉ ሄዱ። ጌታም «እኔም አልፈርድብሽም። ዳግም ሐጢያት አትስሪ» ብሎ ምህረት አደረገላት።

ሰዎችን መክሰስና የሰዎችን ወንጀል መቁጠር ቀላል ነዉ። የኢሕአፓ አባሎች ብዙ ዜጎችን ገድለዋል። መኢሶንም እንደዚሁ። መቼም በደኖንና አርባ ጉጉን የምናስታዉስ አነግ ያደረገዉን እናውቃለን። የደርግንማ እንተወዉ። አቶ ስዬ አብርሃ እራሳቸዉ አባታቸዉንና ሁለት ወንድሞቻቸዉን ደርግ ገድሎባቸዋል። እንነጋገር ከተባለ ፣ ሁላችንም ብንመረመር ወንጀል አያጣንም። የሰዉ ደም ያፈሰሰን ብዙ አለን። ደም ያላፈሰስንም ብንሆንና ጥይት ባንተኩስም ሰዎች ሲገደሉ ዝም ማለታችን እራሱ ተጠያቂ ያደርገናል። እንነጋገር ከተባለ ብዙ ብዙ ማለት እንችላለን።

ነገ ግን ቢበቃን አይሻልም ውድ ኢትዮጵያውያን ? ጣእሙ እንዳለቀ ማስቲካ ያለፈዉን ከምናኝከ በይቅርታ ያለፈዉ ታሪካችንን ወደኋላ ትተን፣ ከዚህ በፊት የተፈጠረዉ ደም መፋሰ ወደፊት እንዳይፈጠር በፍቅር መያያዙ አይሻለንም?

በሶስተኛዉ ምድብ እንደ ሁለተኛዉ ምድብ የነ አቶ ስዬን ድርጊት የሚቃወሙ አስተያየቶችን የያዘ ምድብ ነዉ። ምክንያታቸዉ ግን የተለየ ነዉ። በዚህ ሶስተኛዉ ምድብ ያሉ አስተያየቶች አፍቃሪ ኢሕአዴጎችና የገዢዉ ፓርቲ ካድሬዎች የሚያራገቡት አስተያየቶች ናቸዉ።

ድልወንበሩ ነጋ የሚባሉ አንድ አፍቃሪ ኢሕአዴግ ሰዉ አቶ ስዬ አብርሃ የአንድነት ፓርቲ አባል መሆን እንዳላስደሰታቸዉ አይጋ ፎረም ላይ በወጣዉ ጹሁፋቸዉ «ለምንድን ነዉ የትግራይ ኩሩ ልጅ ስዬ አብርሃ፣ ለትግራይ በቀል አረና ጀርባ ሰጥቶ በምርጫ 97 ጸረ-ትግሬ ቅስቀሳ ሲያደርጉ የነበሩትን የሚቀላቀለዉ ?» ሲሉ ነበር ዘረኛ፣ ጠባብና የኋላ ቀር አመለካከታቸዉን ለማንጸባረቅ የሞከሩት።

በኢሕአዴግ ዉስጥ ችግር ፈጣሪ የሆኑት የአክራሪ ኃያሎች የፕሮፖጋንዳ መጠቀሚያ ነዉ የሚባለዉ አይጋ ፎረም፣ የአቶ ድልወንበሩን ጽሁፍ ከማዉጣቱ አንድ ቀን በፊት «ዛሬ ዶር ነጋሶና አቶ ስዬ የአራና ትግራይን የኦሮሞ ፌደራሊስት ንቅናቄንና የኦሮሞ ሕዝብ ኮንግረስን በማሳጣት ብዙም የማይታወቀዉን የአንድነት ፓርቲ ለመቀላቀል ወስነዋል። አቶ ስዬ አንድነትን መቀላቀላቸዉ አረና ትግራይ በርሳቸዉ ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለዉ ያሳያል» ሲል በአንድነት ፓርቲና በአረና/ኦፌዴን/ኦሕኮ መካከል መከፋፈልን ለመፍጠር ሲፍጨረጨር ታዝበናል።

በመጀመሪያ ደረጃ በምርጫ ዘጠና ሰባት ወቅት ኢንተርሃምዌ በማለትና ቅንጅት የትግራይ ወገኖቻችን ለማጥፋት እንደተነሳ በማራገብ መሰረተ ቢስና አሳፋሪ ፕሮፖጋንዳ ሲረጩ የነበሩት እራሳቸዉ ኢሕአዴጎች ነበሩ።

አንድ ጊዜ በአዲስ አበባ ጸረ-ትግሬ ወረቀቶች ተበትነዉ ነበረ። እነዚህን ወረቀቶች በአዲስ አበባ

እየተሰራጩ መሆናቸዉን የተገነዘቡ የቀድሞ የቅንጅት አመራር አባላት  ይህ ወረቀት እነርሱ እንዳልጻፉትና አጥብቀዉ የሚያወግዙት መሆኑን የሚገልጽ መግለጫ ያወጣሉ። ኢሕአዴግ ለሚቆጣጠረዉ የኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና የኢትዮጵያ ረድዮ መግለጫውን ለሕዝብ እንዲያነብላቸዉ ቅንጅቶች ይጠይቃሉ። ነገር ግን መግለጫቸዉ ሳይነበብላቸዉ ይቀራል።

ይህም የሚያሳየዉ ተበተነ የተባለዉ ወረቀት የመነጨዉ ከኢሕአዴግ እንደነበረና አላማዉን የትግራይ ወገኖቻችንን ከሌሎች ወንድሞቻቸዉ ለመለያየትን በፍርሃት ተሞልተዉ ወደዱም ጠሉም አገዛዙን እንዲደግፉ ለማድረግ ነበር።

እዉነቱ ይሄ ሆኖ እያለ አቶ ድልወንበሩ በቅንጅት አካባቢ ጸረ ትግሬ ቅስቀሳ ተደርጎ ነበር ማለታቸዉ ሰዉዬዉ ተራ የአገዛዙ ካድሬ መሆናቸዉን ያሳያል። የሚጽፉትና የሚያራግቡትም ከእዉነት የራቀና በጥላቻ ላይ ያተኮረ ጊዜዉ ያለፈበት ርካሽ ፕሮፖጋንዳ ነዉ።

አቶ ድልወንበሩና አይጋ በጻፉት ላይ ለማንሳት የምፈልገዉ ሌላም ነጥብ አለ።  አቶ ድልወንበሩ የጻፉት ትክክል ነዉ እንበል። አቶ ድልወንበሩ በኢሕአዴግ፣ መኢአድ፣ የአቶ ልደቱና የአቶ ጫሚሶ ቡድኖች ጋር በሼራተን የተደረገዉን ስምምነት ይደግፋሉ። በዚህ ስምምነት ከአቶ መለስ በስተቀር ሁሉም የቅንጅት አባል የነበሩ ሰዎች ናቸዉ።

ታዲያ አቶ መለስ ዜናዊ ከቀድሞ ቅንጅታዉያን  ጋር በሼራተን ከተጨባበጡ አቶ ስዬ አብርሃ ብርቱካን ሚደቅሳ ከምትመራዉ ፓርቲ ጋር አብረዉ ለመሥራት መወሰናቸዉ እንዴት ሆኖ ነዉ ጸረ-ትግሬ ዉሳኔ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለዉ ? አቶ መለስ ሲያደርጉት ጣፋጭ አቶ ስዬ ሲያደርጉት መራራ የሚሆንበት ምክንያቱ ምንድን ነዉ ?

አቶ ገብሩ አሥራት ድርጅታቸዉ አረና ትግራይ በመቀሌ ባደረገዉ የመጀመሪያ ሕዝባዊ ስብሰባ ወቅት አንድ የማልረሳዉና ልቤን የነካዉ ትልቅ አባባል ተናግረዉ ነበር። አቶ ገብሩ አሥራት በመስቀል አደባባይ በተደረገ አንድ ሰላማዊ ሰልፍ ከሌሎች የተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር በመሆን  በዚያ ንግግር ማድረጋቸዉ ይታወሳል። ያኔ ያደረጉትን ንግግር በማስታወስ አንድ የኢሕአዴግ ካድሬ «የትግራይ ጠላት ከሆኑት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተገኝተዉ ለምን ንግግር አሰሙ?» በሚል ላቀረበላቸዉ ጥያቄ አቶ ገብሩ ሲመልሱ «ኢትዮጵያዉያንን እስከሆንን ድረስ ትግራይ መሬታችን ነዉ። ኦሮሚያ መሬታችን ነዉ። ደቡብ ና ሶማሊያ መሬታችን ነዉ። አፋርም መሬታችን ነዉ። ለነርሱም ትግራይ መሬታቸዉ ነዉ። አማራም ትግራይ መሬቱ ነዉ። ሊኖርበት ይችላል። በዚህ ማመን አለብን። ከዚህ ዉጭ የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶችን እንደጠላት ለማስፈራሪት መጠቀም የሥልጣን እድሜን ማራዘሚያ እንደሆነ መታወቅ አለበት። አሁንም በሰላምዊ ትግል ካመኑትና ሕጋዊ ፈቃድ ካገኙት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር አብረን መሥራት እንቀጥላለን።" በማለት ድርጅታቸዉ ከሌሎች የተቃውሚ ድርጅቶች ጋር አብሮ እንደሚሰራና በኢትዮጵያ የመከፋፈል ፖለቲካ ቦታ እንደማይኖረዉ ነበር ያስረዱት።

ያኔ በመቀሌዉ ስብሰባ በአቶ ገብሩ አሥራት ላይ የተሰነዘረዉ ጥቃት ነዉ አሁን በአቶ ስዬ ላይ እየተሰነዘረ ያለዉ። ነገር ግን አቶ ስዬ ከማንም የበለጠ በኢሕአዴግ ዉስጥ ያለዉን የሚያውቁ እንደመሆናቸዉ በርሳቸዉ ላይ ለሚሰነዘረዉ መሰረተ ቢስ ጥቃቶች አቶ ገብሩ እንደመለሱት ሁሉ በቂ ምላሽ እንዳላቸዉ አልጠራጠርም።

አቶ ስዬና አቶ ገብሩ እንዲሁም ሌሎች ከተቀሩት ኢትዮጵያዊያን  ወንድሞቻቸዉና እህቶቻቸዉን ጋር ለአንዲት ኢትዮጵያ፣ ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባት ፣ ለሰላም፣ ለሕግ የበላይነት፣ ለመልካም አስተዳደር ለመሥራት መወሰናቸዉ ኢሕአዴግ የትግራይን ሕዝብ ከሌላዉ በመነጠል ፣ የትግራይን

ሕዝብ በማስፈራራት ሲያገኝ የነበረዉን ጥቅም ሙሉ ለሙሉ የሚያስቀር፣ የትግራይን ሕዝብ በእጅጉ የሚጠቀም፣ በወንድማማቾች መካከል ፍቅርንና መቀባበልን የሚያመጣ ትልቅ ክንዋኔ ነዉ።

በአድዋ፣ በጉንደት፣ በጉራ .... በአንድ ላይ ስንሆን የጋራ ጠላቶቻችንን አሸንፈናል። አሁንም ትግሬዉ አማራዉ ኦሮሞዉ አፋሩ ሁሉም ወደ አንድነት ሲሰባሰብ አገር ታድጋለች። አንዱ ተበድሎ ሌላዉ አይጎዳም። ሁላችንም በጋራ እናድጋለን። አቶ ስዬና ዶር ነጋሶ የአንድነት ፓርቲን ሲቀላቀሉ ፣ እቶ ገብሩ የመድረክ የሕዝብ ግንኙነት ፣ ዶር መራራ ጉዲና የመድረኩ ሊቀመንበር ሆነዉ ሲሰሩ ማየት ኢሕአዴግ ይዞት የነበረዉ ትልቁ በዘር የመከፋፈል መሳሪያዉ ዋጋ ቢስ እንደሆነበት በግልጽ የሚያሳይ ነዉ።

አይጋ ፎረም እንዲሁ በከንቱ በአንድ በኩል አንድነት በሌል በኩል በአረና/ኦሕኮ/ኦፌዴን መካከል ልዩነት ለመፍጠር እያደረገ ያለዉ ከንቱ ጥረት በተመለከተ ትንሽ ብለን እናቆማለን።

አይጋ የአንድነት ፓርቲን «ብዙ የማይታወቅ» ሲል ፓርቲዉን ለማንኳሸሽ መሞከሩ በጣም የሚያስቅ ነዉ። ፓርቲዉ ደጋፊዎቹና አባላቶች በየክልሉ እየታሰሩበትና እየተዋከቡበት የአገዛዙን በትር ተሸክሞና ችሎ ሕዝብን አሁንም እያንቀሳቀሰ ያለ ጠንካራ ድርጅት ነዉ። ሰማኒያ አራት ጽ/ቤቶች ያሉት ሲሆን በገጠር በከተማ በኦሮሞያ፣ በትግራይ ፣ በደቡብ ፣ በሶማሌ ክልል፣ በአፋር በመላዉ ኢትዮጵያ ጠንካራ ሕዝባዊ መሰረት ያለዉ ድርጅት ነዉ።

ኢሕአዴግ ፓርቲዉ ጠንካራ በመሆኑ ፈርቶና ሰግቶ ሊቀመንበሯን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ሕገ ወጥና ተልካሻ በሆነ ምክንያት በቃሊቲ እሥር ቤት እንድትታሰር ያደረገዉ ለምን እንደሆነ ጠንቅቆ የሚያውቀዉ አይጋ ፎረም፣ የአንድነት ፓርቲ በርግጥ ጠንካራ ፍትሃዊና ነጻ መርጫ ከተደረገ ትግራይን ጨምሮ በሁሉም የአገሪቷ ግዛት አሸናፊ እንደሚሆን ዉስጡ ይገነዘበዋል ብለን እናስባለን።

**ከዚህ በፊት የኢሕአዴግ ከፍተኛ የሆኑ ባለሥልጣናትን አሳምኖና አነጋገሮ በኢትዮጵያዊ አጀንዳዎች ዙሪያ በማሰለፍ የድርጅቱ አባላት እንዲሆኑ ማድረጉ፣ ተራርቀዉ የነበሩ የተለያዩ ድርጅቶች በአንድ ላይ መጥተዉ የኢትዮጵያ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ በማወለብለብ አገር ለማዳን በመድረክ ሥር እንዲሰሩ ትልቅ ሚና መጫወቱ በርግጥ የአንድነት ፓርቲ ያለዉን ጥንካሬ በጉልህ የሚያሳይ ነዉ።**

የነአቶ ስዬ አብርሃ ወደ አንድነት መግባት የአንድነት ፓርቲን ብቻ ሳይሆን መድረክንም የሚያጠናክር ነዉ። አንድነት ተጠናከረ ማለት፣ አረና/ኦሕኮ/ኦፌዴን ተጠናከሩ ማለት ነዉ። በነአረናና በአንድነት መካከል ምንም አይነት ችግር የለም። በመድረክ ዉስጥ አብረዉ የሚሰሩ፣ አብረዉ የሚታገሉ፣የሚተማመኑና አንድ አላማ ያላቸዉ ኢትዮጵያዉያን ናቸዉ። ምናልባትም ወደፊት አንድ ግንባር ወይንም አንድ ፓርቲ ወደ መሆንም የሚሸጋገሩበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ስለዚህ አይጋዎችና መሰሎቻቸዉ ብዙም አትልፉ እንላለን።

ይልቅስ የምታራምዱት የጎሳ ፖለቲካ ያለፈበትና ያረጀበት መሆኑን ተገንዝባቹህ የኢትዮጵያዉያንን ስሜትና ፍላጎት ባንጸባረቀ መልኩ የምትደግፉት ድርጅት እንዲንቀሳቀስ ግፊት ብታደርጉ መልካም ይሆናል። የችግሩ አካል ከመሆን የመፍትሄ አካል ትሆኑ ዘንድ እንመክራለን።

በሚቀጥለዉ ጽሁፍ የነአቶ ስዬ አብርሃ አንድነትን መቀላቀልና የመድረክ ምሥረታ ምን ያህል በአገራችን ትልቅ ለዉጥ ሊያመጣ እንደሚችልና ለምን ኢትዮጵያን በሚወዱ ኃይላት ሁሉ ሊደገፍ እንደሚገባዉ አንዳንድ ሃሳቦችን ለማሳየት እንሞክራለን።

እስከዚያዉ ለሁላችንም ቸር ይግጠመን !